**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!**

# የደም አክሊል

## <u>ትዕይንት ፩</u>

(ሦስት ሕጻናት ከመጋረጃ ውጭ ሻማ ይዘው "ሰማዕታት የዚችን ዓለም ጣዕም በእውነት ናቁ፤ ደማቸውንም ስለእግዚአብሔር አፈሰሱ፤ ስለመንግሥተ ሰማያትም መራራ ሞትን ታገሱ።"(x2))

/በግብዓተ ድምጽ "8ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አንበሳ ውድም ሽንፈት ገጥሟቸው ከሃገር ሸሹ። ሕዝበ ክርስቲያን ስለተስፋ ቃሉ፥ ስለእምነታቸው ተሰደዱ፤ ስለስሙ ትሰደዳላችሁ የተባለውተፈጸመ። በንግሥት ዮዲት ጦር በመጋዝ ተሰንጥቀው፥ በሰይፍ ተመትረው በጦር ተወግተው በመጥበሻ ተጠበሱ። ሕጻናት የእናታቸውን በድን ጡት የሙጥኝ እንዳሉ ተጨፈጨፉ።ገዳማት ፈራረሱ፤ መጻሕፍት ተቃጠሉ። ቤተ ክርስቲያን የሰማዕትነት አክሊል ኑ ቅመሱ እያለች ደወሏን ደግማ ደጋግማ ደወለች።"/..........

ደወል ተደጋግሞ ይደወላል። መጋረጃ ሲከፈት ንግሥት ዮዲት በክብር ዙፋን ተቀምጣ መርዕድ በቀኝ ለገሰ በግራ ደምስ በር ላይ ጦርና ጋሻ ይዞ ቆመው ይታያሉ። ከንግሥት ዮዲት ጎን ካባና ጎራዴ ተቀምጧል።

**ዮዲት፦** /በቁጣ/ ይህ ወንበር የሙሴን ሕግ ያስከብራል። ከእንግዲህ የንግሥትን ወዳጅነት የማየሹትን ሁሉ ቁልቁል ዘቅዝቃችሁ በመስቀል ቆዳቸውን በመግፈፍ አሰቃይዋቸው። /ከጎኗ ያለውን ካባና ጎራዴ ለመርዕድ እየሰጠችው/ እንካ ቀኝ እጄን ተጠቀምበት።

**መርዕድ፦** ንግሥት እነዚህን ውሸታም ክርስቲያኖች ለማጥፋት፥ የሙሴን ሕግ ለማስከበር፥ ሥርዓተ ኦሪትን ለማስፋፋት ቆርጬ መነሳቴን ይወቁልኝ።

**ለገሰ፦** እንግዲህ ንግሥት ይህን ሥራ ሥሩ ካሉን እንደ ካታኮምቦቹ ክርስቲያኖች የመሰየፊያ፥ ከአውሬ ጋር ማታገያ ትርዒት አዘጋጅተን እንደሰት።ሥጋቸውን እየቀረደዱ ሙዳሙዳውን እየቦጨቁ ለኛ ሰዎችድል በማሳየት ለመጥ ለመጥ፥ ጎመድ ጎመድ አያደረጉ ሲበሏቸው እያየን እንዝናና።

**መርዕድ፦**አዎ ንግሥት ጥሩ ብልሃት ነው፤ በቶሎ ይዘጋጅ።

**ዮዲት፥** ጥሩ እንግዲህ፥ የጎራዴያችሁን ስለት ፈትኑት፤ ጩቤአችሁ የክርስቲያንን ገላ ይገፋ እንደሆነ እዩት። ከደነዘዘ ሳሉት። እንዳላችሁት እሳቱም፥ ሰይፉም፥ ጉድጓዱም በፍጥነት ይዘጋጅና በሞታቸው እንሳቅ፤ በእልቂታቸው እንደሰት። በሉ እንግዲህ እናንተም ወደ ክርስቲያን አደናችሁ፣ እኔም ወደ እልፍኜ።

**መርዕድ፦** አተ....ተ....ተ....ተ....ተ....ተ....ተ ዘራፍ! ዘራፍ!

የንግሥትን እምነት ማነው የሚነካው

አንበሳው መርዕድ መኖሩን ዘነጋው

ይቆረጥ አንገቱ ይመተር ይቀላ

ተገፎ ይተልተል የክርስቲያን ገላ

ፎክር ፎክር አለኝ ወኔዬ ተነስቶ

የአይሁድን ጠላት ጭንቅላቱን ሸቶ

ዘራፍ ዘራፍ ልበል ጠላትን ለመምታት

ጎራዴዬን ልሳል ጦሬንም ልስበቃት

ለክርስቲያን ሁሉ ወዮለት ወዮለት

አንበሳው የንግሥት አሽከር መርዕድ መጣለት

*/መርዕድና ለገሰ ወጥተው ሄደው አንዱን መነኩሴ እያሯሯጡት ይታያል። መነኩሴው ብዙ መጻሕፍት ይዞ ይታያል።/*

**መነኩሴው፦** አታገኟትም! አዎ አታገኟትም። ነፍሴን ከሥጋዬ ለይታችሁ ያን ጊዜ ትወስዱታላችሁ። እናንተ ከሃዲዎች መስሏችሁ እኮነው ቤተ ክርስቲያንን ልተጠፉ የምትታገሉት። ግን የኖህ መርከብ ተምሳሌት ቤተ ክርስቲያን አትጠፋም። አዎ ቤተ ክርስቲያን አትጠፋም። /ተንበርክኮ ወደ ሰማይእያየ / ምነው ፈጣሪዬ እውነት ልንጠፋ ነው? ወይንስ ወርቅ በእሳት እንዲፈተን ልንፈተን ይሆን? ምነው ደግነት የተሞላበት ፊትህን ቢመለከቱ? ሲያሳድዱህ ሲያንገላቱህ አንተ እነርሱን ለማግኘት ወደ አነደዱብህ እሳት መንዝህን ዓይነ ልቦናቸውን ብትከፍትላቸውና ቢያዩ ምናለ? ኧረ አንተነትህን አሳያቸው! ማንነትህን ግለጽላቸው። /ከተንበረከከበት መጻሕፍቱን አተኩሮ እየተመለከተ/ እውን የኢትዮጵያ እጅ ይታጠፍ ይሆን? እውን ፀሐይ የሆነች ተዋሕዶ ትደበዝዝ ይሆን? አሁን እነዚህን መጻሕፍትበዋሻ ውስጥ ልሰውራቸው፤ የእውነት አምላክ በፈቀደ ጊዜ ይገለጠው። ዘመን ያውጣው፣ ትውልድ ያግኘው። ከእንግዲህ ማን ቁጭ ብሎ ይጽፈዋል?አባቶች በደማቸው አቆይተው ለእኔ አስረክበዋል። እኔም እንዲሁ አደርጋለሁ። ያውላቸው ሥጋዬ ያሻቸውን ያድርጉት። የቅዱስ ያሬድን አደራ ተሸክሜ ከምሞት ልሰውረው። /ወደህዝቡ ዞሮ/ ልጄ ውርሴን በደሜ አትሜ ልሰውርልህ ነው፤ ይህን ሕይወት የሆነ ቃል ውጥተህ ብላ። አባቶችህ ሞተው ያወረሱህን ሞተህ ለልጅ ልጅህ አውርሰው። የሚበጅህ ስለሆነ ነው በዚህ የሞት አደራ የፈተንኩህ። ልጄ ውርስህ ብትይዘው ያበራልሃል፤ ብትለቀው ግን ሕይወትህ ይጨልምበሃል።

**መርዕድና ለገሰ፦** /በመጋረጃ ውስጥ/ ያዘው . . . . ያዘው . . . . ያውና ከዚያ ላይ . . . . እለፈውና ከፊቱ ቁም!

**መነኩሴው፦** መጡ….መጡ! እነዚህ አረመኔ እምነት በላዎች! እምነቴን ሊወስዷት መጡ። ውርሴን ለያጠፉ መጡ።/መጽሐፍቱን ይደብቃሉ/እንግዲህ ልጄ ሰውሬልሃለሁ።አውጥቶ መብላቱን እወቅበት።አበላሉ ጠፍቶብህ እንዳትሳሳት። ስለአበላሉ አባቶችህን ጠይቅ፤ይነግሩሃል።ሽማግሌዎችን ጠይቅ ያስተምሩሃል። ሽማግሌ ከአንደበቱ ውሸት አትወጣምና። ልጄ አደራ! አደራ! /መርዕድና ለገሰ ይዘዋቸው ይሄዳሉ/

## ትዕይንት ፪

*/መጋረጃ ሲከፈት እዝራ በዋሻ ውስጥ እንደተኛ የአባቱና የልጁ ድምጽ በግብዓተ ድምጽ ይደመጣል።/*

**ሕፃን ልጅ፦** አባ …… አባዬ ……. አድነኝ……

**ሽማግሌ፦** /ጎላ ባለ የስቃይ ድምጽ/ እ…ህ… ጌታ አፍርሶ በሶሥት ቀናት የሠራት ቤቱ አሁንም አትፈርስም። እ…እ… አባቴ የሰጠኝን ሳልለቅ … ለልጄ የተፈተነች እምነትን፣ የደም አክሊልን አወርሰዋለሁ። እህ … ልጄ … እንካ ዳዊቴን ድገመው፤ እንካ መዋስዕቱን ዘምረው። እንካ….. እንደሰጠሁህ በሰማይ እጠይቅሃለሁ። ልጄ… አደራ…. አደራ…..

**እዝራ፦** አባን፣ እማን፣ ባለቤቴን፣ እኔንስ ለማን? መጡ….. መጡላችሁ። ግፈኞች መጡላችሁ። እኔማ እብድ ነኝ። እብድ ሰዉን ማን ይገለዋል? ግን እናንተ በዋሻ፣ በዱር፣ በግበበ ምድር ያላችሁ ሁሉ ከእዉነት ሊያፈናቅሏችሁ መጡ። እዉነትን ሊያሳድዱአችሁ መጡላችሁ። አንቺ ጀንበር ጠልቀሽ እርጂኝ። በቀን ብርሃንሽ ከምታጋልጭኝ በሌሊት በዳፍንት ያዙኝ እያልኩ እንቅፌን ልጣ። ወገን…… እንደ አባትህ ቆዳህን

እንገፋለን እያሉ እኮ አስፈራሩኝ። አባቴ ቆዳዉ ተገፎ መሞቱ በዓይነ ኅሊናዬ እየተመላለሰ ሲታረድ ያየሁት አንገቱ ከዓይኔ ሳይጠፋ እንገድልሃለን ይሉኛል። አቤት ጭካኔ በተገደለ፥ በተገፈፈ ቆዳዉ ላይ ሎሚ ጨመቁበት። ለኔ አሳቢ ክንዱን ጠፍንገው በእንግርግሪት አስረው በሰይፍ ቀረደዱት።

**ሽማግሌዉ፦** (በግብአተ ድምፅ) .... ልጄ እንካ ዳዊቴን ድገመዉ፣ እንካ ያሬድን ዘምረዉ፥ እንካ ዉርሴን ድጓዉን ጠብቀዉ

**እዝራ፦** እንካ ድጓዉን አለኝ እራሱን በሰይፍ መካከል አሳልፎ። ይሁን እኔስ እስካሁን ተቀብዬ አቆየሁት። ከእንግዲህ እኔ እብድ ስባል ወይንም ደግሞ እንደ አባቴ የሞትን ጽዋ ስቀምስ ለማን ነው የማስረክበዉ? እንጃለት ለዉርሱ ! ማን ነዉ እንደ አባባ ዉርሴን አልለቅም በማለት ቆዳዉን የሚገፍ ማናት እንደ እማማ እምነትን ለመጠበቅ ጡትዋን የምትቆረጥ? የትኛዉ ልጅ ነዉ እንደ ማሙሽ አያቱን የሚከተል? እስኪ ንገሩኝ? ለእኛ አይደለም የዚያ ሰዉ ሁሉ ሞቱ? ለዉርስ አይደለም ስደቱ? አቤት! ነጋልኝ። አይሁድ ከሀዲዎች ድጓዉን ሊወስዱብኝ? ማሙሽ .....ማሙሽ ያ ቅብዝብዝ የንግሥት አሽከር የመጣ እንደሆን አልሰጥም ዉርሴን በለዉ። አለቅም ዉርሴን በለዉ። አባቴ ሞቶበታል ። የመንፈስቅዱስ ስጦታ ነው በለዉ።

አ..... ሀ.... ለካስ ማሙሽ ሞተሀል። አየ ልጄ! አንተ ሞተህ አሳበድከኝ? አየ ልጄ! (ቤቴል መጥታ ትቆማለች) .......... ቤቴልዬ እዳያልሙብሽ፣ እንደ ማሙሽ ትሞቺብኛለሽ? ቤቴልዬ ማሙሽ እኮ ጥሎኝ ሄደ! ግን አባም፣ እማም፣ ማሙሽም ባለቤቴም ይህን ዋጋ ጥለዉልኝ አለፉ።

**ቤቴል፦** ወንድም ጋሼ ተዉ እባክህ እነሱን እያሰብክ ጨለማን ስትሸሽ ብርሃንን እንዳትለቅ

**እዝራ፦** ተዉ አልሽኝ ቤቴልዬ? አይሁድ በጦር በጎራዴ ሲያስጨንቁን፣ የነ አባባን አደራ የያሬድን ስጠታ አምጡ ሲሉን፥ ሲያንገላቱን ምኑን ልተወዉ? ቤቴልዬ ሊወስዱብን እያነፈነፉብን ነዉና እንደብቀው። ቤቴል ያን ለገንዘብ ሲል ራሱን ባንዳ ያደረገዉን የዮዲትን አሽከር ለገሠን የእባቶቻችን ዉርስ ነዉ አይበላም በይዉ። መስራቿ ክርስቶስ ስለሆነ ቤተ-ክርስቲያን አትጠፋም በይዉ።

**ቤቴል፦** ወንድም ጋሼ አይዞህ የአባባ ዉርስ እኛ እያለን አይጠፋም ! ይልቅ ያረፉትን ወገኖች እያሰብክ በጭንቀት ህሊናህን አትወጥረዉ። እነርሱ እኮ የእዉነትን መንገድ አልለቀቁም። ማዘንስ እዉነትን እረግጠዉ በሐሰት ለሚጠፉት ወገኖቻችን ነዉ። ወንድም ጋሼ ይልቅ እነ አባባን ስለ እዉነት ብለን እንከተላቸዉ፤ በሕይወታችን እንምሰላቸዉ። ደግሞም የቀረሽኝ አንተ ብቻ ስለሆንክ መሥራት የሚገባንን ሳንሠራ ብትለየኝ ሐዘኔ እጥፍ ይሆናል።

**እዝራ፦** አዎ የቀረሁሽ እኔ ነኝ። ሌላዉ ቀሪሽ ደግሞ ዉርሱ ነዉ። ጠራኝ የጊዮርጊስ መንፈስ፣ ጠራኝ የያሬድ መንፈስ፣ ቤቴሌ ....... ይጠራኛል ማሙሽ ና ይለኛል ልጄ ናፈቀኝ። ማሙሽ አባትህ ና ይልሃል እብድ አባትህ ይጠራሃል። ልጄ ወ/ቂርቆስ ናልኝ ልጄ ና...... የአባትህን ዉርስ እንካ ልጄ ተቀበለኝ አቤት! ብቻዬን አስቀሩኝ? ባለቤቴ ሆዷ ዉስጥ እስካለዉ ሽል እቶን ዉስጥ ተጣለች። ማሙሽ ስጋ ሰዉነቱ ለአንበሶች ተሰጠ።

**ቤቴል፦** እማ ጥሪኝ እማ ሞትሽ ሞቴ ሊሆን ብርሃንሽ ሊያበራልኝ ይጠራኛል ስለ እዉነት ስደትሽን ልቀበል ጥሪሽ ይሰማኛል፤ እማ የከንዲዎች ሰይፍ በአንገቱ ቢዘረጋ ቅርሴን ላላወጣ ከእዉነት መንገድ ወደ ኋላ ላልል አንቺ የቀመስሽዉን የሞት ጽዋ ልቀምስ .....ቃል ለሰማይ ቃል ለምድር...ቅዱሳን አባቶች ለሰማዕትነት ተሹማችሁ በደማችሁ የሕይወት ታሪክን ጻፋችሁ። የድል አክሊልን አገኛችሁ። አባቶች እኔም እንደናንተ የአላውያንን የግፍ ስቃይ በመፍራት ከመንገዳችሁ ላልወጣ ቃል ለሰማይ ቃል ለምድር...አባ! አባዬ! ያሬድን አስታውሽ አትርሽ ስርአትን እንዳትጥሽ ማለትህን አልዘነጋም። ግን እግዚአብሔር እንደጠበቀህ እንዲጠብቀኝ፣ ድል ማድረግን እንዲሰጠኝ ለኔ ለደካማዋ ልጅህ

ለምንልኝ፡፡…አባ? አኩሪ ፍኖትህን ልከተል አንተ ከሄድክበት ከእውነት መንገድ ፈቀቅ ሳልል ቃል ለሰማይ ቃል ለምድር፡፡

## *ትዕይንት ፫*

*/መጋረጃ ሲከፈት መነኩሴው በእስር ቤት ሆነው እጃቸው የኋሊት እግራቸው በሰንሰለት ታስሮ ቁጭ ብለው ይታያሉ፡፡/*

**መነኩሴ፡-** እውነትም አልኩ ጠፈነገኝ ወይ ነገር! ወይ የኔ ነገር! ላውርስ ባልኩ ስቃይ ይሁን ዕጣዬ! ይሁና ግድየለም በደሜ መፍሰስ የክብርን አክሊል እቀዳጃለው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ! ቅዱስ ጴጥሮስ! ቅዱስ እስጢፋኖስ! እግዚአብሔር በዝች በትንሽ ሥራዬ የናንተን የደም አክሊል ሊያድለኝ ነው፡፡ የኔ ሞት የክብር ሞት ነው፡፡ ውርስን እንደጠበቁ መሞት በእግዚአብሔር ፊት ክብርን የሚያሰጥ ታላቅ እረፍት ነው፡፡ የሞት ሞትስ ውርስን መተው ነው፡፡ በራስ መንገድ መሄድ ግን የምትሞት ውዳቂ ሞት ነው፡፡ ልጆች! ይህን ሞት ሽሹት የሞትን ድል መንሻ ትዕግስት፣ ጽናት፣ ምግባር፣ ርትዕት የሆነች ተዋሕዶ እምነታችሁን ያዙ፡፡

**ዮዲት፡-** ጅልነት ነው፡፡ ለመሆኑ ግዜው ሳይደርስ መሲሁ ተወለደ እያላችሁ አይሁደን በእምነታቸው እንዲወድቁ የምታደርጉ እናንተ እነማናችሁ? እረ ከሌላው የተለየ ይህ  ምስጢር የተገለፀላችሁ እናንተ እነማን ናችሁ?

**መነኩሴ፡-** እኛማ በእውነት መሠረት ላይ የታነጽን ርትዕት የሆነች ተዋሕዶን ያመነን የሥላሴ የእጅ ሥራዎች ለመመረጥ የበቃን እድለኞች ነን፡፡

**መርዕድ፡-** ዝም በል! ደግሞ መልስ ይሰጣል ዘልዛላ

**ዮዲት፡-**  ተው ቆይ! እስኪ ይልቅ የእብደት ተግባርህን ትተህ የሰወርካቸውን ዕቃዎች፣ መጻሕፍት ብታሳየን ይሻላል፡፡ አላሳይም የምትል ከሆነ ግን ያለግዜህ በሞት ትቀጣለህ፡፡

**መነኩሴ፡-** እሰየሁ! እሰየሁ! በኃጥአን እጅ በሰማዕትነት ማረፍ እሰየሁ! ስለተስፋ ቃሉ በአላውያን እጅ በሰማዕትነት ማረፍ እሰየሁ! ምንግዜም እኮ ወርቅና አማኝ በእሳት ነው የሚፈተነው፡፡ ንግሥት፡ በስሙ መሰቃየት፣ ስለስሙ መሞት እንዴት ያረካል መሰለሽ…ጌታም እኮ በስሜ መከራን ትቀበላላችሁ ብሎናል፡፡ ስለዚህ ስለስሙ በሰማዕትነት መሞት ሞት ሳይሆን ክብር ነው፡፡ አውጣ የምትሉኝ ዕቃና መጻሕፍት ግን ከአባቴ በውርስ የተቀበልኩት በመሆኑ እኔም ለልጄ የማስረክበው ነው፡፡ስለዚህ ላልሰጣችሁ ባታሰቃዩኝ ጥሩ ነው፡፡ ልቤ የነፍስ ረሃብተኛ እንዲሆን አልፈልግም፡፡

**ዮዲት፡-** ለየቱ ልጅህ? ከሰይፋችን ስለት ለሚያመልጠው? ከዕቶን እሳታችን ለሚተርፈው? አሁን ሌላ ምንም ነገር አልፈልግም ሞትን ወይም ነጻነትን ምረጥ

**መነኩሴ፡-** ዓይን እያላችሁ የማታዩ፣ ጆሮ እያላችሁ የማትሰሙ መሆናችሁን ጌታ በወንጌል አስፍሮታል፡፡

**ለገሰ፡-** እረ ዝም በል ዝጋ?! የንግሥት ጆሮ አይስማህ እባክዎ ንግሥት ይህን ጥጋበኛ እንደ ዶሮ ብልት ገነጣጥለን ለአንበሶች ቅርጫ እንጣለው፡፡ ይዩት እስኪ ልቡ በትዕቢት አብጦ እርስዎን እንኳ ንቆ፡፡

**መነኩሴ፡-** ወንድሜ መድኅን በመስቀል ሆኖ ደሙን ሲያፈስልህ አንተ ግን ያን ያፈቀረህን መድኅን ለመውጋት ጦርህን ሰበቅህ፣ ቀስትህን ገተርህ፣ እሳትን አነደድህ አይደል? እርሱ ግን አሁንም ይፈልግሀል ና ይልሀል፡፡ ሳውልን አድርገኝ በለው፡፡ ሂድና ፈልገው፡፡

**ዮዲት፡-** ውሰደው ሥጋውን ለአንበሶች ስጠው፣ አንበሶች እየቦጫጨቁ ሲቀራመቱት እያየ ወገኔ አይሁድ ይደሰት፡፡

**መነኩሴ፡-** ልጆቼ በጎቼን አደራ! ጠቦቶቼን አደራ! ውርሴን አደራ

**ዮዲት፡-** እስኪ አሁን ወደ ሞት የሚያስጋልባቸው እብደት እንጂ እውነት ፍቅር ነው? ይገርማል! ይህ የሀሳዊ ፍቅር እንዴት ልባቸውን ተነክቷል?

**መርዕድ፡-** ምን አይነት የእምነት ጥንካሬ ነው? ሲዘምቱባቸው የማይዘምቱ፣ ሲገድሏቸው ለገዳዮቻቸው ይቅርታን የሚለምኑ ታድያ እንደዚህ ሆኖ እያየሁ ምን ባደርግ ይሻለኛል? ለምን ከአሁን በኋላ እዘምትባቸዋለሁ…የለም የለም የንግሥት ጆሮ አይስማው…ግን ሁሉም በገደልኳቸው ግዜ ሳውልን ሁን እያሉኝ ያልፋሉ፡፡ ይህ ሳውል የሚባል ማን ይሆን? ዳሩ ለመዳን ጦሬን ወደ ኦፎቱ መቸ መለስኩት…አቤት! በየገዳማቱ መቁጠሪያቸውንና ዳዊታቸውን እንደያዙ ስንቶቹ ረግፈው ቀሩ? ለባዕድ አንገዛም በማለታቸው ስንቶቹ ቤት ተዘግቶባቸው በእሳት አረሩ! አቤት ብዛታቸው (እጁን ዘርግቶ እያየ) አንተ እጅ የስንት ሰው ነፍስ በመዳፍ ውስጥ ይጮሀል፡፡ አንድ ቀን ከሰይፍ ይልቅ እውነትን ትፈልግ ይሆን?

**ለገሰ፡-** ምን እንዳስደሰተኝ ታውቃለህ?

**መርዕድ፡-** ሰይፍ በሚያነሱባቸው ላይ ሰይፍ የማያነሱትን፣ በቀልን በበቀል የማይመልሱትን ክርስቲያኖች ከአንበሶች ጋር ማታገል ይሆናላ ያስደሰተህ፡፡

**ለገሰ፡-** ትክክል ነህ! የክህደት ዝማሬ በአንበሶች ክርን ፀጥ ሲል፣ የአይሁድን እምነት አልቀበልም ብላ በእምቢታ የተንጣጣች ምላስ ጌታ ሆይ! ይቅር በላቸው! ብላ ስትዘጋ አንበሰሶቹ ሙዳ ሙዳ ሥጋቸውን እየቦጨቁ ለንግሥት ድልን በማሳየት ለመጥ ለመጥ፣ ጎመድ ጎመድ እያደረጉ ሲቀራመቱ ከማየት ሌላ የሚያስደስት (የሚያረካ) አለ ትላለህ?

**መርዕድ፡-** ጌታ ሆይ ይቅር በላቸው አለ አልከኝ! ምን አይነት ጠላትን ማፍቀር ነው?

**ለገሰ፡-** ቀልደኖች በላቸው! ይቅር በላቸው ብሎ ነገር…ይልቅ ራሳቸው ይቅር ተብለው በምድር ላይ ቢኖሩ ይሻላቸው ነበር፡፡ ይልቅ መርዕድ ንግሥት እንዳሉህ በብረ ዳሞና በአቅራቢያው ያሉትን ገዳማት በስለት ጎብኝ ሥልጣንህም ጣራ ደርሷል፡፡ መችም ወዳጅ ሲሾም እንደማየት የሚያስደስት ነገር በዚች ምድር የለም፡፡ በል እንግዲህ ወዲያው ሂድ መቸም በነሱ ዘንድ በትር ማንሳት፤ መከላከል ብሎ ነገር የለም፡፡ እንደደረስክ እንደጎመን መቀርደድ ነው፡፡

**መርዕድ፡-** ይሁና እነርሱም ከእምነታቸው ፈቀቅ ላይሉ እኛም ላንራራላቸው ተያይዘናል፡፡ በል እሺ ቻዎ

**ለገሰ፡-** ወደዚያው ልታዘግም ነው?

**መርዕድ፡-** አዎ ወደዚያው መሆኑ ነው

**ለገሰ፡-** ቆይ ቆይ እስኪ ቀደም በተደረገው አሰሳ አንዲት ወጣት ክርስቲያን ከእብድ ወንድሟ ጋር በተራራው ስር መኖራቸው ተረጋግጧልና ወደ እነርሱ ሄደን ብንይዛቸው አይሻልም?

**መርዕድ፡-** እሺ ጥሩ እንሂድ

## ትዕይንት ፬

**ቤቴል፡-** (ቁጭ ብላ ወደ ተመልካች እያየች) አንቺ መሬት የትኛው ዓይነት ነሽ? ኮረኮንች ወይንስ ለም? ነጭ ነቀዝ ደግሞ በውስጥሽ ፈልቷል፤ ቢዘራብሽ ታፈሪ ይሆን? የአባቴን ዘር ይዤ ነበር፣ ልዘራብሽ ፈለግሁ ግን ግን የአባቴ ዘር እንክርዳድ የማያበቅል መሬት ይሻል፡፡……ኡፍ! ባለአደራነት እንዴት ያስጨንቃል ያውም የሕይወት አደራ መጠበቅ፡፡ ግን እኮ ይህ አደራ ሕይወትን የሚሰጥ አደራ ነው፡፡ ዓለም ፈጥና ታስውባለች ታከስምማለች፣ ታበቅላለች ታጠፋለች፡፡ ነገር ግን የእውነት አደራ ለመጠበቅ ይህችን ዥንጉርጉር ዓለም ጥሎ መቅበዝበዝ ከድሎት ወደ ስቃይ መግባት የወደፊት ብርሃንን እያየ እና ተስፋ እያደረጉ ፍጥነትን ወደዚያ መጨመር እንዴት ያረካል (ደወል ይሰማል) አቤት ይሰማኛል…የሰማዕታት ጥሪ ሲያስተጋባ…አንቺ ጀንበር ንጋት ነሽ ስልሽ ልትጠፊብኝ ነው፡፡ ገና እኮ አልጠገብኩሽም፡፡ ገና የማወርሰውን የአባቴን ዘር ማስቀመጫ ሳላዘጋጅ ተዋሕዶ በሰማዕታት ደም ፈንጥቃ ሳታበቃ ሁሉም ሳይመገባት ልትጨልምብኝ ነው፡፡

**ለገሰ፡-** እስኪ ተመልከት በሐሳዊ ፍቅር ጭንቅላቷ ነውልሎ ሃብትን መተው፣ እንደአውሬ እየተቅበዘበዙ ዱር ለዱር መኖር፡፡ ደግሞ እኮ የሚገርምህ የዚያ የቱጃር ከበርቴ ልጅ ነች እኮ

**መርዕድ፡-** የየቱ? የአገረ ገዢው ልጅ ነች እንዳትለኝ!

**ለገሰ፡-** ታዲያስ በባለፈው አሰሳ የንግሥት ወዳጅ አልሆንም አርፌ የያዝኩትን እየገዛሁ አልኖርም በማለት ከሀብት ድህነትን፣ ከከተማ ዋሻን በመምረጥ በአይሁድ እምነት አላምንም ሲል በሓሳዊ ፍቅር ጭንቅላቱ ነውልሎ ሲያስቸግር የተገደለው እኮ ነው፡፡

**መርዕድ፡-** ወይዳ የዚህ ሰው ነፍስም ለካ በመዳፌ ውስጥ ትጮሀለች፡፡

**ለገሰ፡-** እሺ የኛ መናኝ ይነሱአ!… ተነሽ እንጂ! አንቺን እኮ ነው!… ስሚ አንድ ምርጫሽን እፈልጋለው እሳትን ወይም የንግሥትን እምነት

**መርዕድ፡-** እህቴ የንግሥትን ወዳጅነት ንቀሽ ገና ባልተወለደው ተስፋ ባታደርጊ ጥሩ ነው፡፡

**ቤቴል፡-** ካልተወለደው የተወለደ እና ስለኛ የሞተውን የፍቅር ባለቤት ማመን ምን ዓይነት ደስ የሚል  ሕይወት መሰለህ!

**ለገሰ፡-** አሀ! ከንግሥት እምነት ሞትን መረጥሽ?……በኔ እጅ የሰማዕትነት አክሊል ፍለጋ ከሆነ በዚህ ጎራዴ ቀረጣጥፌሽ ያሻሽውን ተስፋ አግኝ!

**መርዕድ፡-** ቆይ ተዋት፡፡ ስሚ ሁለት ምርጫ እሰጥሻለው፡፡ ክርስትናሽን ትተሽ የንግሥት ወዳጅ በመሆን በኦሪት ሕግ ጸንተሽ ትኖሪያለሽ? ነው ወይስ እንዲህ የጎሰቆለ ሥጋሽን ለሰይፍ አሳልፈሽ ትሰጫለሽ?

**ቤቴል፡-** በፍጹም! የኔ ወንድም አይሆንም ክርስቶስ ለኔ ብሎ እንደሞተልኝ ስለኔ ክብር ብሎ ስለቆሰለልኝ ለፍቅሩ፣ ለመቁሰሉ፣ ለቸርነቱ፣ ስታሳርዱት ለመታገሱ ብሰየፍ (ብቃጠል) እንዴት ያረካኛል መሰለህ፡፡ እምነትን ሳይክዱ ውርስን እንደጠበቁ በአባት መንገድ እየሄዱ መሞት እንዴት ደስ ያሰኛል መሰለህ? ይልቅ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፡፡ አሁን እሚጠራህ አለና ሳውልን አድርገኝ በለው፡፡

**ለገሰ፡-** ተነሽ ንስሽ እሳት ነው፡፡ መርዕድ ከዚች ከማታምን ጋር ክርክርን መግጠም አያስፈልግም፡፡ ደግሞም እኮ ንግሥት  ያዘዙንን አንዘንጋ፡፡

**ቤቴል፡-** እሄዳለሁ ልቀቀኝ ድሮም ቢሆን ከሰማያዊ ሞት የምድርን ሞት መርጬ ነው ከዓለም የወጣሁት፡፡ ሞተ ሥጋ ኢምንት ነው፤ ይልቅ አንተ መፍራት ያለብህ ሰማያዊ ሞት ነው፡፡

**እዝራ፡-** ዛሬ ደግሞ በነዚህ አውሬዎች ሰይፍ የሚወድቅ ተረኛ ክርስቲያን ማን ይሆን፡፡ እስኪ ቤቴልዬ እንድትጠነቀቅ ልሂድና ልንገራት፡፡ ከእንግዲህ እኮ በዚህ ምድር ያለችኝ መጠጊያ እህቴ እሷ ብቻ ናት፡፡……ታድያ ያለ ግዜዋ እንዳይነጥቁኝ ልንገራት፡፡

ቤቴል…….ቤቴልዬ……የት ነሽ…… እህቴ…….ቤቴል አንቺም እንደ እማማ! እኔ እኮ እብድ ነኝ ማን ያብላኝ የእናንተን እብድስ እናንተው ካልቻላችሁኝ ማን ይችልልናል ብላችሁ ሄዳችሁ፡፡ እህቴ አንቺም እንደ ማሙሽ አንገትሽ ሊከተፍ በፍጹም አይሆንም ስቃዩን አትችይውም፤ አባም እማም ማሙሽም ባለቤቴም ሰማዕታት ሁላችሁ ደማችሁ ጎልቶ ይታየኛል፡፡ የአደራ ፊደላት በደማችሁ አሰፈራችሁልኝ፡፡ ግን ቤቴል አንቺስ አደራሽን ተወጣሽ፤ ለእኔስ ማነው አጋሬ፣ ማነው አለሁልህ የሚለኝ ……… ባዶነት ይሰማኛል………ቤቴል ሰይፍ አትፈራም፤ ክርስቲያን ናት፤ ሰይፍ አትፈራም፡፡ ቤቴል የሥጋ ብርሃኗ ጨለመ፤ የነፍስ ብርሃኗ ግን ለዘለዓለም ያበራል፡፡…… ነጋላችሁ እናንተ ክርስቲያኖች፡፡ ታዲያ ማን ነው በነአባባ የደም መዝገብ ላይ የሚሰፍረው፣ ማነው የአምላኩን አርዓያ የተከተለው፣ አባባን ሕያው የሚያደርግ፣ ለውርሱ የቆመ ማን ነው? ለአባባ ውርስ ትሞታላችሁ? እንሞታለን፣ እንመስልሃለን ይሉሃል አባባ! ቤቴል …….እርሷ እንደሞተች እኛም እንሞታለን ይሉሻል ፡፡

## ትዕይንት ፳

*/መጋረጃ ሲከፈት አባ ሳሙኤል፣ ሚስታቸው ወ/ሮ ልኬ፣ ልጆቻቸው አስቴርና አብነት ተቀምጠው አስቴር እሳት ለማንደድ ስትጣጣር ትታያለች፡፡/*

**ወ/ሮ ልኬ** ፡-ተይው ልጄ በተስፋ ይነዳል ብለን አንጀትሽን አስቃተትንሽ አይደል፤ ተይው ልጄ ተይው ፡፡

**አብነት** ፡- ተያት እማ ታንድደውና የተኮራመተ አንጀታችንን ታፍታታው ፡፡ ግን እማ ስደት ማለት ሐሳብ ማለት ነው እንዴ? እኔ እኮ ከብዶኛል፡፡ በፍጹም መታገስ አልቻልኩም፡፡ አባባስ ምን አለበት ገንዘብ ይዘህ ብትመጣ ቅጠል እየበላን የቦይ ውሃ እየጠጣን እስከመቼ እንቆያለን፡፡

**አባ ሳሙኤል፡-** ልጄ ግዜው የመሬት ነው፡፡ መሬት ደም ልትጠጣ ብስባሽ ሥጋን ልትበላ አፏን በከፈተች በዚህ አስከፊ ሰዓት ክርስቲያን ለሆነ ሁሉ ጥጋብ የለውም፡፡ አይዞህ ይህ የስደት ጊዜ እስኪያለፍ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ የዘለዓለም ደስታ ነው (ወደ ሕዝብ ዞሮ ) ልጄ አስቴር ይህ የማየው ቡቃያ ምነው አልደረሰም፤ የአሁኑ ገበሬ እንኳ ወቅት ያይ ነበር ፡፡

**አስቴር፡-** ነበር አባባ! ነገር ግን ይህ የምታየው ዘር ለም መሬት አላገኘም፡፡ ደግሞም እኮ የባለቤቱ አይደለም፤ ጠላት አውቆ የበተነው እንጂ፡፡ ጥሩ ዘር የመሰለ ስንት አሳሳች ሞልቷል መሰለህ አባባ፡፡ ግማሹ አሜኬላ ላይ ወድቆ እየቀጨጨ ነው፣ ግን ይጠፋል፡፡ ግማሹ ደግሞ ዓለም አንቆ ይዞታል፤ ቀሪውን ደግሞ ነጭ ነቀዝ ተነስቶ እያነቀዘው ነው፡፡

**ወ/ሮ ልኬ፡-** አይ ይኽ ማሳ ጣጣው የባለቤቱ ልጅ ነበር፡፡ ግን ልጁ ሁሉ የአባቱን ትቶ እንደገና እኔ አዲስ ነው የማዘጋጀው ማለት ጀምሮል ፡፡ የአባቱን የማይከተል ከንቱ ትውልድ፡፡

**አብነት፡-** አባባ ደብራችን እኮ ተቃጠለ፡፡ ከእንግዲህ የት እየሄድን ልናስቀድስ ነው፤ ግን እሱ የቤትህ ቅንአት አቃጠለኝ እያለ ለምን ማራቸው?

**አስቴር፡-** ኸረ እንዲያውም አባም ይህን ሁሉ እውቀታቸውን እንደያዙ ደብሬን አለቅም በማለት በነደደ እሳት ውስጥ እያሸበሸቡ ገብተው ተቃጠሉ፡፡ ታዲያ አባባ እኛስ ለምን እንፈራለን? ለምን እንደነርሱ አንቃጠልም፡፡

**አብነት፡-** አባዬ እነዚህ አይሁዶች ሲዘምቱብን እኛስ ለምን አንዘምትባቸውም? ለምን አንገድላቸውም?

**አባ ሳሙኤል፡-** ልጄ ጌታ በወንጌል ግራ ፊትህን ለሚመታህ ቀኝህን አዙርለት፡፡ክፉውን በክፉ አትቃወም፡፡ አትግደል በቀል የኔ ነው ይላልና እርሱ ግፋችንን ተመልክቶ ብድራችንን ይመልስልናል፡፡ ደግሞ አባም እኮ አልሞቱም አሉ፡፡

**አብነት፡-** አባዬ የታሉ? ንገረኝ አባባ! አባ የታሉ?

**አባ ሳሙኤል፡-** መጻሕፍትን እያሳዩ እኚሽው አባ፡፡ በስጋ ከኛ ቢለዩም ያልሞተ ታሪክ አላቸው ታሪካቸው በፍቃደ እግዚአብሔር ለፍተው ደክመው የጻፉትን የደጎሱትን መጽሐፍታቸውን አስረክበውናል፡፡ እውነታቸውን÷ እምነታቸውን÷ ፍቅራቸውን÷ ትህትናቸውን በልባችን ቀርጸው አልፈዋል፡፡ እና ልጆቼ የቅዱሳን ሞት እረፍት ስለሆነ ሞቱ ልንል አይገባም፡፡

**አብነት፡-** ታድያ አባባ እኛስ እንደአባ እኔ የቂርቆስን÷እማማ የኢየሉጣን÷የጊዮርጊስን÷ ሶምሶን÷ ካሌብና አስቴር ደግሞ የአናንያን÷የአዛርያን÷የሚሳኤልን ÷የሰማዕትነት አክሊል በዮዲት እጅ ለምን አንቀበልም?

**አባ ሳሙኤል፡-** ልጆቼ አባቶቻችን እኮ እኛን ተክተው ነው ያለፉት፡፡ እኛስ ዘር ሳንተካ አባቶቻችን የሰጡንን ዘር ሳንዘራ እንዴት እንሙት? እሺ. እኛስ ሞትን (ወደ ህዝቡ ዞረው) ይህ ቡቃያ አይፈርድብንም እንዲሁ ለነጭ ነቀዝ ትተነው ስንሄድ አያሳዝንም? ልጆች የነ አትናቴዎስ የሕይወት አደራ አለብን፡፡ ቡቃያው ማደግ ሲሻ ለነጭ ነቀዝ ትተነው ብንሄድ ያጠፋዋል፡፡ ልጆች ከእንግዲህ እኔና እናታችሁ አርጅተናል፡፡ከእንግዲህ ለእናንተ አውርሰን የምናልፍበት ግዜ ነው፡፡ልጆች … ይህ ሕይወትን የሚሰጥ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለዓለም የታሪክ አሻራ የሆነ ውርስ በአባቶቻችንናበእኛእንደዳበረ እናንተም መቅረዝ ሆናችሁ እንድታበሩ፡፡አደራ አለባችሁ፤የዕለተ አርብ አደራ፤የቅዱስ ያሬድ አደራ፤የሐዋርያት አደራ፤የሊቃውንት አባቶች አደራ፤…ልጆች አደራ ለጠባቂው መታመን ሲሆን ለሚተወው ግን የባዶነት ነጸብራቅ ነውና ያዙት፡፡

**ሶምሶን፡-** /ከመድረክ ውጭ ቆይቶ/ ጴጥሮስ መስቀልህ ወዴት አለ? ጳውሎስ መሰየፍህ የት አለ? እስጢፋኖስ መወገርህ የት አለ?... አቤት ስለ ብርሃን ስንቶች ጠፉ! ወዳጄ እንኳን በመጥበሻ እንደአሳ ተጠበሰ! መነኮሳቱ ሁሉ አለቁ! ገዳማቱ ተዘረፉ! የዘጉ አባቶች እንደዘጉ ተቃጠሉ!ነደዱ! ብናኝ ሆኑ! ነፍሳቸው ግን ወደ ሰማይ ተነጠቀች! በክብር ተቀመጠች! አጌጠች! አቤት…. ጭካኔ! አቤት ግፍ! የሰማዕትነትን ደወል ለሕዝበ ክርስቲያን እየደወሉ፥ ነጋሪት እየጎሰሙ፥ መለከት እየነፉ፥ የስንቱን አንገት ቀሉት፥ የስንቱን ገላ ገረፉት! አይግፍ! አይጭካኔ! ነገስ ደግሞ እነማን ይሆኑ ተረኞች! የሞት እድል ባለ ጽዋዎች! /ወደ መድረኩ እየገባ/…. ሞትን በሞት ልታሸንፍ ለድል የቆማችሁ ወገኖች እሰየው በሉ፡፡ለክብሩ ዘምሩ፥ ደስ ይበላችሁ፥ እልል በሉ፡፡

**አባ ሳሙኤል፡-** ልጄ አሁን በእኛ ዘንድ ደስታ የለም ውርሳችን ተቀባይ አጥቷል፡፡ የእኛ ደስታስ የደከምንለት ውርስ ተቀባይ ሲያገኝ ነው፡ ይልቅ አረፍ በልና እርምህን አውጣ፡፡

**አስቴር፡-** አባባ እርምህን አውጣ የምትለው የልጁን ነገር ….

**ሳምሶን፡-** ምን ሆነ ልጄ? አስቴር፡የግፈኞችን ሰይፍ ቀመሰና ሞተ?

**አባ ሳሙኤል፡-** ረጋ በል ልጄ! ልጅህን ለእናቱ ማሳመኛ ሲሉ በፊቷ በመፍጫ ፈጩት፤ይህ ሁሉ ስለ ጌታ ስም ነውና አይዞህ ተጽናና፤ ልጅህ ደግሞ የቂርቆስን ፈለግ በመከተሉ ደስ ሊልህ ይገባል፡፡

**ሳምሶን፡-** እንዴት ሆኖ አባባ?አይደረግም? ታሪኩ መሞት የለበትም እሱስ ታሪኬን የማኖርበት ማጎደሬ ነው፡፡ ደግሞስ ያለጋ ሰውነቱ እንኳን ወፍጮ ዱላ ይችላል አባባ ታሪኩ እኮ እንቡጥ ነው ታሪኩ እኮ ገና ልጅ ነው፡፡

**ካሌብ፡-** [ከመድረክ ጀርባ ሆኖ] አቤት አቤት ሞኝነት ገና ለገና የተስፋ ቃልን በማመን አንገትን ለሰይፍ አሳልፎ መስጠት፣ ከተንደላቀቀ ቤት ወጥቶ ስቃይ፣ ከጥጋብ ርሃብ ለምን እኔ ግን አላደርገውም? ለምን ብዬ (ከመድረክ ገብቶ ሶምሶንን እያየ) አሃ! አንተ ጨካኝ እዚህ አለህ ልጅህ ዓለምን ሳይጠግባት አስገደልከው አይደል; ልኑር እያለ በኩልታፋ አንደበቱ ሲማፀን መኖርን ከለከልከው። ሞት ሳይቀርባት ሚስትህ ለሞትዋ ቆርጣ አስገደለችው። ጨካኝ ነህ በጣም ጨካኝ!

**ሶምሶን፡-** ተወኝ! ልጄን እወደዋለሁ ጌታዬንም አፈቅረዋለሁ! ከመውደድ ደግሞ ማፍቀር ይበልጣል። በዝች ምድር ተሰቃይቶ ከሚኖረው እንኳንም አረፈና ወደ አምላኩ ሄደ።

**ወ/ሮ ልኬ፡-** ተው ልጄ ካሌብ! እነርሱ መቼ ሞቱ? በክርስቶስ የሞቱ ሰዎች አረፉ ይባላል እንጂ ሞቱኮ አይባልም። ከዚህ ዓለም ኑሮአቸው በእረፍት ሞት ቢገቱም በሰማይ ግን ሕያዋን ናቸው። የዚህ ምድር ኑሮ ደስታ ግን በሰማይ ይጨልማል። ስለዚህ የወዲያኛውን ነው መሻት።

**ካሌብ፡-** ኤድያ! እንዲያ እያላችሁ ነው ተስፋን ያጨለማችሁት።

**አባ ሳሙኤል፡-** በሉ ሌላውን ነገር ተዉት። እንግዲህ ልጆች እስከዛሬ የእናንተን እንዲህ መሰባሰብ ነበር ስጠብቅ የቆየሁት፤ ዛሬ ግን እንዲህ ተሰባሰባችሁ ስላገኘኋችሁ ውርሴን የማስረክብበት የመጨረሻ ቀን ይሆናል። ልጆች ይቺ ተዋሕዶ እምነታችን ለዘለዓለም እንዳበራች ትኖራለች። የተዘራው ዘርም የእግዚአብሔር ስለሆነ ጠላት ቢያጭደው አያልቅም፣ ቢቀጥፈውም ያቆጠቁጣል። የኛ ሞት ለኛ የማይጠፋ ብርሃን ይሰጠናል እና ልጆች በብርሃናችሁ አብሩ።ብርሃን ሳለላችሁ ተመላለሱ ብሎናልና። (ድጓውን ያነሱና) ይህ ድጓ የቅዱስ ያሬድ የመንፈስ ስጦታ ነው። እንካ ሶምሶኔ የበኩርነትህን ሥራ ሥራበት፣ ሙትለት አደራ ውርሴ እንዳይጠፋ። (ስንክሳሩን ያነሱና) እንቺ ልጄ አስቴር ይህ ስንክሳር የቅዱሳን አበው ታሪክ ነው ራስሽን ከእርሱ አስቀድሚ። (ዝማሬውን ያነሱና) እንካ ልጅ አብነቴ ይህም እንዲሁ የቅዱስ ያሬድ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው ለውርሱ አንተነትህን መስዋዕት አድርግለት። አደራ ልጆች፣ አደራ ውርሴን አደራ

**አስቴር፡-** አባባ ሞትህ ሞት ሳይሆን ብርሃን እንዲሆን የመዳንን ብርሃን በውርስ ስጦታ ለዓለም እንዳበራ ብርሃንን ሰጠኸኝ አባባ አንተ የቀመስከውን ሰማዕትነት እኔም ሳልፈራና ወደኋላ ሳልል እንድቀምሰው ከክርስቶስ ጽናትን ለምንልኝ። የክርስቲያን ሞትኮ የክርስትና ምሥጢር መፍቻ ቁልፍ ነው። በሰማዕትነት መሞት እንዴት ያረካል?

**አባ ሳሙኤል፡-** አዎ ሌላው ደግሞ ልጆች ይህች ከግራ ከቀኝ የተሰበቀባት ተዋሕዶ እምነታችን የእኛ ሰንሰለት መሰላላችን ናት። ብንሞትላት ታበራለች፤ ብንሞትባት ደግሞ አትጠፋም፣ የእኛ ሞት ግን ለመጪው ትውልድ ምስክር ነው። እና ልጆች ከእምነታችሁ ስትሸሹ የፊተኛውን የክርስትና የአባቶቻችሁ መሠረት አጥብቃችሁ እንደ አባቶች ብትጸኑ  የክርስቶስ ተካፋዮች ትሆናላችሁ። (ፊታቸውን ወደ ካሌብ አቅንተው ሃይማኖተ አበውን በማንሳት) ልጄ ካሌብ እንካ ሃይማኖተ አበው ለአንተ አብርተህ ለዓለም ለኩሰው። ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ አድምቀህ አብራው። በአንተ ትጋት የአባቶችን ታሪክ አሳውቅ። አክብረው ያስከብርሀል፣ ሙትለት ሕይወት ይሰጥሀል።

**ካሌብ፡-** ሞታችሁ ላያጠግበኝ፣ ችግራችሁ ላያስደስተኝ፣ ህይወት እያለ ሞት፣ ደስታ እያለ ሃዘን የምታፈሩ አይናችሁ በሞት ጭንብል የተጋረደ እምነት እያላችሁ እግሬን በአጉል ሰንሰለት አስራችሁ እድገትን እንዳላድጋት ኑሮን እንዳልኖራት አንቆ የያዘኝ እርሱ ነው። ይልቅ አባባ ይህንን የእምነት ሰንሰለት ፍታልኝ፤ ነፃ አድርገኝ። በነፃ ህይወት መኖር እፈልጋለሁ። ይህንንም ከዓለም አገኘዋለሁ።

**ሳምሶን፡-** እብደት ቢጤ ይዞሃል እንዴ? ወይስ በጤናህ ነው? የማውቅህን ያክል እንደማላውቅህ አደረግከኝ እኮ!

**እዝራ፡-** /ከመድረክ ውጭ/ ይህ ሊሆን ግድ ነውና አትደንግጡ፤ ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው። በዚያን ግዜ በመከራ አሳልፈው ይሰጡአችኋል፡፡ ይገድሉአችኋል፤ ስለስሜም በአሕዛብ ዘንድ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ። ወዮላችሁ ክርስቲያኖች ለበጎች የማያዝኑ ጨካኞችና ተኩላዎች መጥተዋልና።

**አስቴር፡-** ማነው በዚህ ሞት በበረከተበት ወቅት የጌታን ቃል በአደባባይ የሚሰብከው? ማነው ግን ሥጋውን ጠልቶ ክርስቶስን የወደደ?

**እዝራ፡-** /ከመድረክ ውጭ/ ወገን አሁንስ አፈም ደረቀ እንጀቴም እህል አጣ፡፡ ልብሴም በላዬ ላይ ተቦጫጨቀ። የጌታን ቃል አክብራ የኖረች እህቴን ቤቴልን ሚሚን አንድደው ገድለው እኔን በብቸኝነት ረሃብ ቀጡኝ፡፡ ግን ቤቴል እማ ነች ነይ ያለችሽ? ይገድሉሻል ብላ አስባ እንደሆነ ግን እብድንስ የሚገለው የለም ወይ በያት። /ወደ መድረኩ እየወጣ/ እንደምን አረፈዳችሁ አንቴ ደህና ናችሁ አረመኔ ሲያሳድዳችሁ ነጋባችሁ? ሚጢዬ ግን መሸባት፡፡ አስቴርዬ የአንትሽ ልጅ መሸባት፤ የሞት ጉጠት ካጠገቤ ነጥቆ ወሰዳት፡፡ አስቴርዬ እንደልጅነትሽ ልታጫውትሽ መጥታ ጓዳ ውስጥ እንደሆነች እይልኝ፡፡

**አስቴር** ፡- አይዞህ ወንድም ጋሼ፤ ቤቴል እኮ አልሞተችም ሕያው ነች።

**እዝራ** ፡- አንቺም እንደቤቴል ወንድም ጋሼ አልሽኝ አስቴሬ? እንደኔ ብቻሽን ከመቅረት ያድንሽ!

**ካሌብ** ፡- እስኪ ተመልከት አባባ ሞታችሁ ጤና ሳይሆን አሳብዶት ሲያንከራትተው እያያችሁ ታዲያ እኔም እንደርሱ እንዳብድ ነው ፍላጎታችሁ።

**እዝራ** ፡- ካሌብ እኔ እብድ ነኝ? እኔ እኮ እዝራ ነኝ አታውቀኝም እንዴ? አንቴ እኔ እብድ ነኝ? አስቴር እኔ እብድ ወገኖቹ በሰው ያለቁበት ብቸኛ እብድ ሊባል ይገባዋል እንዴ ወገን? እነዚያ ጨካኞች ያለረዳት ብቻዬን ስላስቀሩኝ እብድ መባል አለብኝ? እብድስ እነዚያ ከሓዲወች! እብደት እኮ ክህደት ነው፡፡ ታድያ እኔ እዝራ እብድ እኔ እብድ! /እያለ ወጥቶ ይሔዳል/

**አብነት** ፡- እማማ እኔ ከእዝራ ጋር ሄጄ የሚበላ ቃርሜ ልምጣ፡፡

**ልኬ** ፡- ተው ልጄ ያገኙህ እንደሆነ ይገድሉሃል!

**አባ ሳሙኤል** ፡- ይሂድ ተይው! እኛስ ባዋቂ አንጀታችን ቻልነው፡፡ እሱ እንዴት ይችለዋል እንዲያውም እስካሁን መቆየቱ ያስመሰግነዋል፡፡ ሂድ ልጄ ሂድ አይሁዶችን ብታገኝ እንኳ ሞትን አትፍራ፤ ይግደሉህ ከርሃብ ሞት ይሻላል፡፡

/አብነት ወጥቶ ይሔዳል/

**ካሌብ** ፡- በሉ እሺ እኔ ልሔድ ነው።

**ልኬ** ፡- ተው ልጄ ካሌብ የአባትህን ውርስ ተቀበል፡፡ ይህን ውርስ በኋላ ብትፈልገው አታገኘውም፡፡ ሽማግሌ አባትህም በመጨረሻ ዘመኑ ረግሞህ እንዳይሞት፡፡ ልጄ ስለ ጠባኸው ጡቴ ብለህ ውርሱን ተቀበል!

**ካሌብ** ፡- እማማ የኔ ውርስ እናንተ የምትሉአቸው ተራ ነገሮች ሳይሆኑ አንደላቆ ሊያኖረኝ የሚችል ጥላችሁት የመጣችሁት ሰፊ ርስታችሁ ነው፡፡ አባባ እኔ የምፈልገው ገንዘብህን እንጂ ይህን ተራ ጽሑፍ አይደለም፡፡ ይህን የእጅ ጽሑፍህን ለሌላ ሰው አውርሰው ፡፡ በሉ እሽ ቻዎ/ወጥቶ ይሄዳል

**አባ ሳሙኤል፡-** ተው ልጄ ተመለስ፤ የዴማስን የጥፋት መንገድ አትመልከት፣ ተው ተመለስ (ዋሽንት)

**ሳምሶን** ፡- አበባ ወንድሜ ሲሰናከል ዝም ብዬ ማየት የለብኝም፡፡ እኔም የጌታዬን ፈለግ በመከተል ነፍሴን በወንድሜ መመለስ ለውጬ በሞቴ ከሄደበት ከጥፋት መንገድ እመልሰዋለሁ፡፡

**አስቴር፡-** አበባ እኔም ክርስቶስ እንደሞተልኝ ስለወንድሜ ሕይወቴን አሳልፌ ሰጥቼ ወንድሜን ከጥፋት መመለስ፣ ከእሳት ማውጣት፣ መንገድ ከሚመስል ከተሰበረ ድልድይ ፈጥኜ ማውጣት አለብኝ።

**ልኬ፡-** ኧረ ተዉ ልጆቼ፣ አግኝተው እንዳይገድሏችሁ።

**አባ ሳሙኤል፡-** ተይ እንጂ እንዲህ ዓይነት ቃል ከአንደበትሽ አይወጣ! ጎሽ ልጆቼ ሂዱ ከአጠገባችሁ ያለውን ወንድማችሁን ወዳችሁ ስለጥፋቱ ካልሞታችሁለት ያላያችሁትን አምላክ አፈቀርንህ እንሞትልሃለን ብትሉት ምን ዋጋ አለው። በእግዚአብሔር ላይ መቀለድ ነው የሚሆን፤ እና ልጆቼ (ሃይማኖተ አበውን አንስተው) እኔን ሆናችሁ የአባትህን ውርስ እንካ በሉት፤ አደራ ልጆቼ /ልጆች ሲሄዱ/

**ልኬ፡-** በሉ ደህና ሁኑ ልጆቼ! እግዚአብሔር በሰላም ይመልሳችሁ፤ ስትሄዱ ተጠንቅቃችሁ ነው። እንግዲህ ምን አደርጋለሁ እንቅፋት እንኳን እንዳይመታችሁ የምሳሳላችሁ እናታችሁ በሞታችሁ ጨክኜ ሰደድኳችሁ። ግን ይሁን ወንድማችሁ በነፍሱ ከሚሞት የእናንተ በሥጋ መሞት ይሻላል።

**መርዕድ፡-** /ከመድረክ ውጭ/ በደብረዳሞ እና በአካባቢው የነበሩትን መነኮሳት እንደ ንግሥት ትዕዛዝ ፀጥ ረጭ አደረኳቸው። ድምጥማጣቸውን አጠፋኋቸው። አቤት የፋሰሰው ደም! አሁን ደግሞ በየዋሻው ያሉትን እንዳድን ታዘዝኩ፤ አዎ የንግሥት ትዕዛዝ ነው፣ መፈጸም አለብኝ፤ አለበለዚያ እኔም ታዳኝ እሆናለሁ /ወደ መድረኩ ሲገባ መጋረጃይ ዘጋል፤ ሲከፈት ልኬና አባ ሳሙኤል ተሰይፈው የጣጥራሉ። አባ ሳሙኤል መፅሀፍ ቅዱስ ገልጠው የሐዋርያት ሥራ 9÷1 ያለውን ቃል አውጥተው/

ል ……. ልጁ ጌታ…….. ይቅር እንዲልህ ……….ን ……. ንስሐ ግባ። ሰይፍን ጥለህ ተከተለው፤ እውነቱ ይበራልሃል፤ …እ…. እንካ አንብበው (መርዕድ ተቀብሎ የሐዋርያት ሥራ 9÷1-16 ያነብና)

**መርዕድ፡-** ሳውል ማን ነው? ንግሩኝ አባቴ ሳውል ማን ነው? ማን ይነግረኛል? ሳውል ምንድን ነው?

**አብነት፡-** /ቃርሞ እየተመለሰ ከመድረክ ውጭ/ እኔስ በልቼ ጠገብኩ እህል አጥቶ የቆየ የእማማና የአባባ አንጀት ትንሽ እንኳ እንዲንቀሳቀስ ይህችን ዳቦ ልውሰድላቸው። /ወደ መድረክ ይገባና/ አባባ፣ እማማ የት ነው ያላችሁት /ወለል ወድቀው ሲያይ ይደነግጥና/ አባባ ምነው ኧረ እማዬ ብቻዬን እኮ ነኝ አባባ? ኧረ አይቻልም ተነሱ የሚበላ ይዤላችሁ መጥቻለሁ፤ እንኩ ብሉ አባ ማን ያኑረኝ እማዬ ጅቡ ሲጮህ ከማን ጋር ልተኛልሽ ነው።

**መርዕድ፡-** (ከጎዳ በመውጣት) ማሙሽ ሳውል ማን ነው ንገረኝ?

**አብነት፡-** አልፈልግም ዞር በልልኝ! አንተ ነህ አይደል ያረድካቸው፤ አትጠጋኝ፣ ዞር በልልኝ ከዚህ፣ እንደ አባባ ልታርደኝ ነው እማማን እንደ አረድካት ልታርደኝ ነው? አልፈልግም ዞር በልልኝ። /እያለ ወደ ኋላ ያፈገፍጋል)

**መርዕድ፡-** ልገድልህ አይደለም ማሙሽ፤ እንካ የእናት እና የአባትህን ደም በግፍ እንዳፈሰስኩ የእኔም ደም በአንተ እጅ ይፈሰስ። /ስይፉን ይሰጠዋል/ ግን ማሙሽ ሳውል ማን ነው? /አብነት ሳይፋን ተቀብሎ ሊገድለው እጁን ሲዘረጋ የአባቱ ቃል በግብአተ ድምጽ ይሰማል/ "ልጁ ጌታ በወንጌል ግራ ፊትህን ለሚመታህ ቀኝህን አዙርለት፤ ክፉን በክፉ አትቃወም፣ አትግደል፣ በቀል የእኔ ነው ይላልና እርሱ ግፋችንን ተመልክቶ ብድራታችንን ይመልስልናል።" /ይህን ቃል ሲሰማ አብነት ሰይፉን ጥሎ ከእናቱና ከአባቱ አስከሬን ላይ ይወድቃል፤ መርዕድ መጽሐፉን ሲገልጥ የሐዋ 9÷1-16 ያለው ቃል በግብአተ ድምጽ ይነበባል/

**መርዕድ፡-** አሁን ሳውል ጳውሎስ መሆኑን በእውነት አወቅሁ፤ እያየሁ አለማየቴን ተረዳሁ። በግፍ የገደልኳችሁ ወገኖቼ ፈጣሪ ይቅር እንዲለኝ አማልዱኝ፤ ብርሃናችሁ በእኔም ላይ እንዲያበራ ከፈጣሪ ለምኑልኝ።

## ትዕይንት ፮

**ካሌብ፡-** /ቤት ውስጥ ተቀምጦ/ አቤት! ከዚህ በላይ የሚያስደስት ምን ነገር አለ፤ በአባቴ ሀብት ላይ ያለ ምንም ተቀናቃኝ አዛዥ ናዛዥ ሆንኩ። ብቻ ምን ያደርጋል! አባቴ በስተርጅናው እንደ አልባሌ ዕቃ ወደቀ። እነርሱ እንኳ የራሳቸው ጉዳይ፣ ግን ያንን ሕፃን የት አግኝቼ ይችን ዓለም ባጠገብኩት። እነርሱ እንደሆኑ ካደሩበት አይውሉም፣ ከዋሉበት አያድሩም። ለማንኛውም አሁን ወደ ጌታ ለገሠ ዘንድ ልሂድና የአባቴን ውርስ በሙሉ ማግኘቴን ላረጋግጥ።

/ለገሠ ከመጋረጃው ውጪ ቆሞ እያለ የዮዲት አዋጅ ቃል ከመጋረጃ ውስጥ ይደመጣል/ *"ሕዝቤ ሆይ የአይሁድን እምነት ክዶ በሐሳዊ ፍቅር ልቡ በኖ ለትዕዛዜ አልገዛም ብሎ የክበለለውን የቀድሞ ሹሜን መርዕድን ይዞ ለመጣ ትልቅ ስጦታ ይሰጠዋል፤ የመርዕድን ቦታ ይዞ ያስተዳድራል። ሹም ለመሆን ሹምን ማስያዝ!"*

**ለገሠ፡-** /አዋጁን ከሰማ በኋላ/ በዚህ ሰሞን ንግሥት እንዴት ያለ ማለፊያ አዋጅ አወጁ አዎ! ብላ ሲሉት ካልበላ ለሚበላ ቦታውን መልቀቅ አለበት ገና ለገና ጓደኛዬ ነው ብዬ ለምን ብዬ ሹመት ያምልጠኝ። ካለበት ጉድጓድ ምሼ በማውጣት አንጠልጥዬ አቀርበዋለሁ።

**ካሌብ፡-** /ከውጪ ይመጣና/ ጤና ይስጥልኝ ጌታዬ

**ለገሠ፡-** ኡፍ መጣህ እንዴ ጥሩሰዓት አክባሪ ነህ ስማ ካሌብ አሁን በአይሁድ እምነት ለማመንህ እና ራስህን ወደ እምነቱ ለማስገባትህ በምን ማረጋገጫ ልመንህ።

**ካሌብ፡-** ይመኑኝ እንጂ ጌታዬ ይህን ሁሉ የማደርገው እኮ የንግሥት ፍቅር ይዞኝ ነው።

**ለገሠ፡-** እመነኝ አልክ . . . . /ፊቱን ወደ ኋላ ዞሮ/ የማላውቅ መሰለህ! የነዛ ተፈላጊ ቀንደኛ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ወራሽ አይደል ሞኙን ይፈልግ! ጥሩ ግን አንድ ነገር ልፈትንህ እፈልጋለሁ ትስማማለህ?

**ካሌብ፡-** ይፈትኑኝ ጌታዬ ለንግሥት ስል የማልከፍለው መስዋዕትነት የለም። ግን የአባቴን ርስት አደራ።

**ለገሠ፡-** ለእርሱ ግድ የለም ለእኔ ጣለው ይኸውልህ አሁን በአካባቢያችን ድጓ፣ ስንክሳር፣ ሃይማኖተ አበው . . . . የተባሉ መጻሕፍትን ደብቀው በመዞር ሰላምን የነሱን ሁለት ሰዎች አሉ እነሱን ከነመጽሐፍቶቻቸው በእጃችን ውስጥ ካስገባህልን ያልከው ሁሉ ይደረግልሃል ያለበለዚያ ግን ታዳኝነትህ ይጸናል ገባህ ?

**ካሌብ፡-** እህቴን ወንድሜን /ወደ ተመልካቹ ዞሮ/ . . . .ምን አደርጋለሁ እነርሱም ታዳኝነቱ ላይቀርላቸው እኔስ ለምን የአባቴ እርስት ያምልጠኝ . . . .ጌታዬ ባሉኝ ነገር ተስማምቻለሁ ነገ በ9 ሰዓት ከተራራው ጀርባ ያለውን ዋሻ ያውቁት የለ እዚያ ሁለቱንም ቁጭ አድርጌ እጠብቆታለሁ።

**ለገሠ፡-** አዎ ደምስም እኔም እናውቀዋለን አሁን ሂድ ባልከኝ ሰዓት እመጣለሁ። ቂል ለገንዘብ ብሎ ዘመዶቹን ለእሳት አሳልፎ የሚሰጥ ደግሞም እኮ ያን ያለውን የአባቱን እርስት ለእኔ ለላቤ ዋጋ ተሰጥቶኝ ወስጄዋለሁ። ከአፌ የገባውን ሥጋ ማን ያወጣል ለሁሉም ጊዜው ይድረስ።

**ካሌብ፡-** /ዋሻው ውስጥ ተቀምጦ/ ከእንግዲህ ዙረው ዙረው ፈልገው ሲያጡኝ ተመልሰው ከዚህ መምጣታቸው አይቀርም ስለዚህ ከዚህ ቁጭ ብዬ ጠብቄ ሲመጡ ማስያዝ ነው፡፡

**አብነት፡-** /ከጓዳ ወጥቶ/ ካሌብ አባዬ እና እማዬ እኮ ሞቱ ብቻዬን ጥለውኝ ሄዱ፡፡

**ካሌብ፡-** አይዞህ እኔ አለሁልህ፡፡ አሁን ወደ ጓዳ ግባ ምንም ዓይነት ነገር ብትሰማ እንዳትወጣ፡፡

**ሶምሶን፡-** አስቴር ወንድማችንን ፈልገን አጣነው፡፡ ከዚህ በላይ ካገኙን ጥሩ ስለማይሆን ወደ ዋሻው እንመለስ፡፡ ሞታችን ለክብር ቢሆንም ማውረስ የሚገባንን ሳናወርስ ማለፍ የለብንም የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ደግሞ ከዚያው እናገኘዋለን፡፡

**አስቴር፡-** ጥሩ እንግዲያውስ ወደ ዋሻው እንመለስ፡፡

**ካሌብ፡-** የመኖሬ በር ተከፈተች፡፡ መጡ፤ እንግዲህ ሽፍጥ ልጀምር ያዘንኩ መስዬ ቁጭ ከዚያ ይዞ መቅረብ ነው፡፡ አይዞህ ካሌብ ድፈር መኖር በእግሩ ዳዴ እያለ መጥቷል፡፡

**አስቴር** ፡- /ወደ እርሱ እየተጠጋች/ የእናቴ ልጅ ወንድም ጥላ ከዚህ አለህ እንዴ? እኛ እኮ አንተን ለመፈለግ ያልሔድንበት ቦታ የለም!!

**ካሌብ** ፡- ምነው እንዲህሞት በበዛበትና በረከሰበት ሰአት መጣችሁ? እኔም እኮ ስለእናንተ እያሰብኩ በጣም ተጨንቄ ነበር፡፡

**ሳምሶን** ፡- ወንድሜ በሰይፍ መካከል አልፈን የመጣነው የአባባን የውርስ መጽሐፍ ልንሰጥህ ነውና እንካ ስለእግዚአብሔር ብለህ ተቀበለን/ መጽሐፉን ይሰጠዋል፡፡

**ካሌብ** ፡- እሺ እቀበላለሁ፡ ተቀብሎ ይስመዋል፡፡

**አስቴር** ፡- የመንከራተታችን ዋጋ ሆኖ እግዚአብሔር ያንተን ልብ አራራልኝ! ለውርሳችንና ለፍቅሩ ተገዥ ሆንክ በል ከእንዲህ ውርስህ እንዳይጠፋ፡ በከንቱ እንዳይቀር ቃል ግባለት፤ በከንቱ እንዳይቀር ሙትልት፤ የአባትህን አደራ ለልጅህ አስረክበው፡፡ ና ስለደስታችን እቀፈኝ፤ ደስ ብሎኛል፡፡ /ይተቃቀፋሉ/ ሳምሶን አባባና እማማን የደስታችን ተካፋዮች ይሆኑ ዘንድ ከጓዳ ጥራቸው፡፡

**ካሌብ** ፡- እነርሱማ ከንቱ ሀሳብ እያዉጠነጠኑ በንግሥት ሰይፍ ተሰይፈው ሞቱ!

**ለገሰ** ፡- ካሌብ

**ካሌብ** ፡- /ከእነርሱ እየሸሸ/፡ ዞር በሉ! ውርስ ውርስ እያላችሁ ሕይወቴን እንዳታበላሹት!

**ሳምሶን** ፡- /ለገሰና ካሌብን እየተመለከተ/ ለካስ ባንዳ ኑረሀል እንደ ዮሴፍ ትሸጠን! የአባባን ታሪክ ልታጨልም ብርሃኑን ልትገታ አሰብክ አይደል? ለእኛስ ተወው ሞታችን ክብራችን ነው፡፡ አንተ ግን እንዲህ በወደድካት ዓለም ፀንተህ እንደማትቆይባት እወቅ፡፡ ጨካኝ ነህ እምነትህን አደራህን ሽጠህ የበላህ ይሁዳን ነህ፡፡

**ለገሰ** ፡- ዝምበል ዝጋ........ ጥሩ ነው ካሌብ ከእንግዲህ የንግሥት ወዳጅነትህ ተረጋግጦልሃል፡፡ መጽሐፍቱን ተቀብሎ ሁለቱንም ወደ እስር ቤት ይወስዳቸዋል፡፡

**አብነት** ፡- /ከጓዳ ወጥቶ/ ወንድሜ እህቴ ከጅብ ማስደንገጥ ከብቸኝነት አዳኑኝ ስል ይህ ሰው በላ አሳልፎ ሰጣቸው፡፡ አባ ተመልከት ስስታም ልጅህን፤ እማ ተመልከች እምነትሽ በጡት ነካሽ ሲመረዝ፤ አባ ጥራኝ አባዬ አንተን የወሰደ ሞት ይውሰደኝ! መሰየፍ ያግኘኝ /ተንበርክኮ/ ምነው እግዚአብሔር አምላክ

ቂርቆስን በሰማዕትነት የጠራህ ምነው እኔን በብቸኝነት ከስቃይ እንደ እርሱ አልጠራ አልከኝ ጨክንክብኝ /ይቀመጣል/፡፡

**እዝራ** ፡- /ከመድረኩ ውጭ/ አስቴሬ መሸባት የአጎቴ ልጅ መሸባት፤ ወንድም ለወንድም ጨክነ፤ አስቴሬ ዮዲትን እምነታችንን አንክድም በያት! ሳምሶኔ ቤተ ክርስቲያን ጾኑ ዓለት ስለሆነች አትጠፋም በላት! እርጉም በላት ሞት በሥጋ ለክርስቲያኖች ተራ ነገር ስለሆነ እብዱ እዝራ አይፈራሽም በላት፡፡

**አብነት** ፡- /ከተቀመጠበት እየተነሳ/ ዕዝራዬ አትለየኝ ብቸኛ ነኝ፤ ዘመዶቼን ካሌብ በላቸው፡፡ ግን ለምን የማያምን አማኝን ያጠቃዋል?

**እዝራ** ፡- ሰማሁ አብነቴ የአባትህን ውርስ ወሰዱት አይደል! አትረቡም በላቸው፡፡ እስኪ ተመልከቱ ይህን እንበጥ ገና በለጋነት ዕድሜው እንደእኔ ብቸኛ ሲያደርጉት፤ ጨካኝ ነሽ በላት! አብነቴ ህፃኑን ልጅ በቻዬን ስላስቀረሽኝ እግዚአብሔር ፍጥረት ይንሳሽ ማኅፀንሽ ይረር በላት ዘር ያሰጣሽ በላት አብነቴ አጎቴን የጨለማ ጉም ዋጠው፡፡ እናትህን የጅቦች ሰይፍ በላት፡፡ አስቴርንና ሶምሶንን ወንድማቸው በላቸው፡፡

አረመኔ! እምነት በላ ነህ አትረባም በለው፡፡ ርስት አገኘለሁ ሲል ዘመዶቼን አስፈጃቸው አይደል አትበላውም በለው፡፡ ወንድሞቼን በግፍ አስገድሎ በግፍ ሊበላ! በፍጹም አይችልም፤ ሄጄ በማቃጠል እንዳልነበር አደርገዋለሁ፡፡

**አብነት** ፡- ወንድም ጋሼ እንዳይገድሉህ እንጂ እንዲያ የኀጓለትን ሃብት አሳጥተህ እራቁቱን አርገው፡፡ እንሒድና አሁን ሁለታችን እናቃጥለው፡፡ /ወጥተው ይሄዳሉ/

/ካሌብና ለገሰ ከመድረክ ውጭ/

**ለገሰ፡** ስማ ካሌብ እንቅጩን ልንገርህ የአባትህን ሃብት ለእኔ የልፋት ዋጋ ተብሎ በበላይ አካል ተስጥቶኝ ወርሸዋለሁ፡፡ ነገር ግን ባደረግከው ተጋድሎ መጠለያና ትንሽ ገንዘብ ይሰጥሃል፡፡ መታደን ግን ከአሁን በኋላ ቀርቶልሃል፡፡

**ካሌብ** ፡- ምነው ጌታዬ የአባቴን ሀብት ለምን? ኧረ ይተው ጌታዬ?

**ለገሰ** ፡- ዝጋ በቃ! ሌላውን ሁሉ እርሳው አለያ በእጄ ነህ! ሆዳም ስግብግብ ሊበላ! መርዝ ብላ!

**ደሞስ** ፡- /በጣም እየጨኸ/ ተቃጠለ! ተቃጠለ! ጌታዬ ተቃጠለ!

**ለገሰ** ፡- ምን?

**ደሞስ** ፡- ተቃጠለ ምንም ነገር የቀረ የለም፡ ተቃጠለ!

**ለገሰ** ፡- ምኑ ነው የተቃጠለው?

**ደሞስ** ፡- ሁሉም ነገር አንድም የቀረ ነገር የለም!

**ለገሰ** ፡- የምኑ ሁሉ ነገር ነው? እረጋ በል!

**ደሞስ** ፡- በባለፈው የወረሱት ሃብት ሁሉ ተቃጠለ፡፡

**ለገሰ** ፡- ማነው ያቃጠለው?

**ደሞስ** ፡- እሱንማ ባውቅ እኔስ መቼ እለቀው ነበር፡፡

**ለገሰ** ፡- ያ ካሌብ የሚሉት ከሓዲ የት ነው ያለው?

**ደሞስ** ፡- እሱ ከዛ እሳቱን ለማጥፋት ይታገላል እርሱ ባይኖርማ ሁላችንም ተቃጥለን . . . . . .

**ለገሰ** ፡- ነፍስ ሥጋው ይቃጠልና! እኔ እዳልበላው ነው ያቃጠለው፡፡ የእሱ ተንኮል ለእኔ ጠፍቶኝ ሒድ አሁን በፍጥነት ይዘኸው ና በቁሙ እንዳለ በእሳት አቃጥለዋለሁ፡፡

**ደሞስ** ፡- አ ……ሀ ለካ ይኸም አለ! ጌታዬ ይህን ደብዳቤ አንዲት አሮጊት ናቸው የሰጡኝ፡፡/ለገሰ ደብዳቤውን ሲከፍት በግብአተ ድምፅ/

"ውድ ወንድሜ ሆይ አፈር ከማቡነን ከሕጻነት ጊዜአችን ጀምሮ በንግሥት ቤት ተቀምጠን ባንዳ በመሆን የክርስቲያንን ደም እስከማፍሰሳችን የነበረውን ጊዜ አስበው፡፡ ውድ ወንድሜ ያ ያሳለፍነው የጨለማ ጊዜ የባንዳነት ዘመን በጣም አስጠልቶኝ አንገፍግፎኝ፣ ያ ያፈሰስነው የንጹህ ወገኖች ደም እረፍት ነስቶኝ ክርስቶስ የጠፋውን በግ እኔን ፈልጎ ስላገኘኝ እሱም ተደስቶብኝ እኔም ተከትዬው ሄጃለሁ፡፡ ወንደሜ ሆይ ይህ ጊዜያዊ ደስታ ነገ በዋይታና በጩኸት ይተካል፡፡ ለማለት የፈለግኩት አንተም እንደእኔ በሠራኸው ስራ ተፀፅተህ በክርስቶስ አምነህ ብትመለስ ጥሩ ነው፡፡ ዛሬ የእኔ መዳን ሲያስደስተኝ የአንተ እንደጠፋህ መቅረት ደግሞ በጣም እያሳዘነኝ ነው፡፡ እና ወንድሜ ወደ አዳኝህ ተመለስ፡፡ ያፈሰስከው የብዙ ንጹሃን ደም እንደ አቤልና እንደ ዘካርያስ ደም ፍረድልኝ እያለ በእግዚአብሔር ፊት እየጮኸ ነው፡፡ ሌላው የምልህ ነገር ቢኖር ባለፈው ከሁለት ክርስቲያኖች ተቀብለህ የወሰድከውን መጽሐፍ ላክልኝ፡፡ ብትመለስ ጥሩ ነው፡፡ ባትመለስ ግን መጽሐፍቱን በእኔ ለውጠህ ለንግሥት አቅርበኝና ስልጣንን አግኝ፡፡ እኔ ግን ከአሁን በኋላ በሰማይ ተሹሜአለሁ፡፡ መጽሐፍቱን ስትልክልኝ ያን ጊዜ እመጣለሁ፡፡ መዳን ሰይፌን አስጥሎኝ የክርስቶስ እንደራሴ የሆንኩና ክርስቶስን የመረጥኩ ወንድምህ መርዕድ ነኝ ከዋሻው፡፡"

**ለገሰ** ፡- ሀብት አመለጠኝ ስል ሌላ ስልጣን መጣ! እንዲህ ነው እንጂ ልፋትን ሲቆጥር! ለእነዚያ ተራ ነገር በሆኑ መጻሕፍት እራሱን ለውጦ ከመጣ ምን ገዶኝ በደስታ እቀበለዋለሁ፡፡ ከዚያ በኋላ የንግሥት አሽከር ለገሰ ተብሎ ከተነገረ አቤት ሀብት… አቤት ክብር አቤት ክብር ብቻ እንጃ እስኪደርስ ቸኩያለሁ፡፡

**ደምስ፡-** /በጥፊ እየመታው/ አንተ አስመሳይ ቀጥል! ቀጥል!

**ካሌብ፡-** ድሮም ላትረቡኝ አይሁድን ማመኔ

**ደምስ፡-** ምንም ዓይነት ቃል አያስፈልግም፤ ዝም ብለህ ብትሄድ ነው የሚሻልህ!

**ለገሰ፡-** መጣህ አንተ ከሃዲ! እኔ እንዳልጠቀምበት ነው አይደል ያቃጠልከው በል ቆይ ማንነቴን አሳይሃለሁ፡፡ ደምስ! በል ፈጠን በልና ከዘመዶቹ ጋር ወስደህ ጠፍንገው፡፡ ስትመለስ ከእርሱ እህትና ወንድም የቀማናቸውን መጻሕፍት በሙሉ ይዘህልኝ ተመለስ፡፡

**ደምስ፡-** /መጻሕፍቱን እየሰጠ/ ይኸው

**ለገሰ፡-** በል ከዚያ ዋሻ ሂድና እነኝህን መጻሕፍት ሰጥተህ ያን ከኃዲ ይዘኸው ና

**ደምስ፡-** የቱን ከኃዲ?

**ለገሰ፡-** መርዕድን ነዋ! በፍጥነት ይዘኸው ና እኔም እቤት እጠብቅሀለሁ

## ትዕይንት ፯

/መጋረጃ ሲከፈት እዝራ፣ መርዕድና አብነት ዋሻው ውስጥ ይታያሉ፡፡/

**መርዕድ፡-** እዝራ እናትና አባትህን፣ ወንድምና እህትህን፣ ልጅህንና ሚስትህን ገድዬ ብቻህን ስላስቀረሁህና ለዚህ ሁሉ ችግር ስለዳረግሁህ ፀፀት የእግር እሳት ሆኖ እያቃጠለኝ ነውና እባክህ ይቅር በለኝ፡፡

**እዝራ፡-** ማሙሽን ከእኔ ከአባቱ መለየት ሳይወድ ለይተኸው፣ ባለቤቴን ቅሪት እያለች ከእቶን ውስጥ አነደድካት አባባን ቆዳውን ገፈህ፤ እማማን እናቴን ጡቷን ቆርጠህ፣ ቤቴልን በእሳት በማቃጠል ናላዋን እንዳዞርከው ለአንተ ለነፍስ በላው ይቅርታ! ላደርግልህ?ገድለኸኝ እያየሁ እንዴት ብዬ ይቅር ልበልህ? ዘመዶቼን ሁሉ ስለገደልካቸው ይቅርታ… የማይሆን ነገር ነው፡፡ /ወጥቶ እየሄደ/ ዘመዶቼ አስታወስኳችሁ፤ ትዝታችሁ ቀሰቀሰኝ፡፡ ማሙሽ የኔ ልጅ ናልኝ፤ ቤቴልስ ለምን አትመጭም አልናፈቅሽም እንዴ?

**መርዕድ፡-** ማሙሽ የእናት የአባትህን ደም በማፍሰስ አንተን ብቻህን እንድትቀር በማድረግ ስለ በደልኩህ አንተ እንኳን ይህን ጊዜ በሕይወት እያለህ ከልብህ ይቅር በለኝ፡፡

**አብነት፡-** ይቅርታ የማደርግልህ የአባባን የውርስ መጽሐፍ ስትሰጠኝ ነው፡፡

**መርዕድ፡-** ለእርሱ ከሆነ ምንም ችግር የለም፤ ማሙሽ የመምጫው ጊዜ ዛሬ ነው፡፡ እስከዚያው ግን አንተ ከጓዳው አትውጣ!

**ደምስ፡-** አንተ ከሀዲ እንደ እኔ እንደኔ ይገፔ ብገድልህ ነበር ፍላጎቴ ጌታየ ለገሰ ያዘዙኝን አልጥስም፡፡ መጽሀፍቱን እየሰጠ እንካ ያዝና እንሂድ፡፡

**መርዕድ፡-** /መጻሕፍቱን ተቀብሎ/ መጣሁ እሽ ጠብቀኝ /ጓዳ ውስጥ ይገባና/ ማሙሽ እንካ ውርስህን እንካ፣ ሀብትህን ኑርበት እኔም እውነትን አውቄ ስለእውነት መስዋዕት ልሆን እየሄድኩ ነው፡፡ ለካ እነኛ አባቶች በሞታቸው ይደሰቱ የነበረው ለእውነት መሞት እለሚያስደስት ነው በል ማሙሽ በይቅርታ ሸኘኝ፡፡

**አብነት፡-** እግዚአብሔር ይስጥልኝ እርሱ ይቅር ይበልህ፡፡ እሳቱን ውሃ፣ ሰይፉን ለምለም ያድርግልህ፡፡ እኔ ይቅር ብዬሃለሁ፡፡ /መጻሕፍቱን እያየ/ አባባ እንዳበራልኝ ውርስህን አደራ ብለኸኛልና እኔም አልጥለውም፤ አንተ በሥጋ ብትሞትም ብርሃንህን ሰጥተኸኛልና ለእኔና ለመሰሎቼ እስከ ዘለዓለም እያበራ ይኖራል፡፡

## ትዕይንት ፳

/በእስር ቤት ውስጥ ሶምሶን፣ አስቴር፣መርዕድና ካሌብ የኂሊት ታስረው ለገሰና ደምስ ቆመው ሲጠየቁ ይታያል/

**ለገሰ፡-** /አመድ በእጁ ጨብጦ እያሳያቸው/ የቂሳርን ወዳጅነት ጠልተው በክርስትና እምነት ተሞልተው፣ ሞተልን፣ ተሰደደልን፣ ቅብጥርስ ምንትርስ እያሉ ዓይናቸው እያየ ወደ ሞት ጉጠታችን በመግባት በእቶን እሳት የነደዱ የእናንተ ሰማዕታት የነዛ ከሀዲያን ብናኝ ( አመዱን እየበተነ) አመድ ይህችን አለም በብናኝነት መሸኘት /ወደ ሳምሶን ዞሮ/ የእኛ ታሪክ አሳተላላፊ ወገኛ ከእኛ አምልጦ ለሚኖረው ለየትኛው ልጅህ ነው ታሪክ የምታስተላልፈው፡፡

**ሶምሶን፡-** እውነት ትመነምናለች እንጂ አትጠፋም፤ ስለምድር ሀብት የሞቱ ሁሉ እጥፍ ሞትን ሞቱ፤ እኛ ግን ለሞተልን ሞትን፣ ያፈቀረንን አፈቀርን፣ ሞታችንም ደስታ የሰፈነበት ቀና መንገድ ነው፡፡

**ለገሰ፡-** /ወደ መርዕድ ዞሮ/ የእኛ ለእምነት ክብርን ሕይወትን ሰጭ?ወገኛ! ለመሆኑ ምን አጠጡህና እንደዚህ ሆንክ?

**መርዕድ፡-** ወዳጄ እርሱ የለበስከወው ምድራዊ ካባ ነገ ያልቃል፡፡ይህ አምሮ የሚታየው ሰውነትህም ረግፋል፡፡ በክርስቶስ ስለ ክርስቶስ መሞት ግን ለዘለዓለም የማያልፍ ጸጋን ያሰጣል፡፡እና ወንድሜ የክርሰትናን መንገድ መከራውን አይተህ አትጥላው፤ ቅመሰውና አጣጥመው፤ትረካበታለህ፡፡

**ለገሰ፡-** በቃህ አትዘላብድ

**አስቴር፡-** ምንድን ነው እንዲህ የምታስጨንቀን! በሞታችን የቀረጥን ሰዎች እኮነን፤ ለምን አትገድለንም? ግደለን? እግዚአብሔርን ካልፈራህ ግደለን፡፡

**ለገሰ፡-** ቀስ በይ አትቸኩይ ለመሞቱ ትደርሽበታለሽ፡፡

**ዕዝራ፡-** /ከመድረክ ውጭ/ ሞትን ሻትኩ! ለዘመዶቼ የመጣ ሞትን ወደድኩ በቃኝ! በቃኝ! ፀሐዩ፣ ብርዱ፣ ረሀቡ፣ መራቆቱ አንገፈገፈኝ! በቃኝ ከእንግዲህ አልደብቅም! /ወደ እስር ቤት ሄዶ/ አሰቴር አስቃዩሽ? ሶምሶን አንገላቱህ? ይታያችሁ! ወገን ይታያችሁ! ሰዎች በስቃይ እንዲህ ተፈትነው ሲያልፉ፡፡ ተዋሕዶ ግን አለች፤ ለወደፊትም ትኖራለች፡፡ በየጊዜው የተነሱ ከሃዲያን በፍጹም ሊያጠፏት አልቻሉም፡፡ ወደፊት የሚነሱትም ሊያጠፉት አይችሉም፡፡ ይኸው አሁን የአጎቴ ልጆች ተሰቃዩ፤ ወደፊትም የክርስቲያን ወገኖች ሁሉ ስለ እምነታቸው ይሰቃያሉ፡፡ /ፊቱን ወደ አስቴር አዙሮ ጣቱን ወደ ለገሰ በመቀሰር/ ይህንን ባንዳ የንግሥት ሉሌ እውነት አንበሳ ውድም እየመጣነው በላት፡፡

**ለገሰ፡-** ማንን ልታስፈራራ ነው አንተ እብድ!

**ዕዝራ፡-** ያችን የሴት አለቃህን ጉዲትን ከአንቺ ጋር ካለው ከእኛ ጋር ያለው ይበልጣል በላት፡፡ የክርስተያን ጦር ያሸንፋል በላት፤ የቤተክርስቲያንንና የኢትዮጵያን ታሪክ ልታጠፊ አስበሽ ከሆነ ጠብሽ ከእግዚአብሔር ጋር ነውና አይሆንልሽም በላት!

**ለገሰ** ፡- ሌላስ የለህም!!

**እዝራ፡-** /ወደ ካሌብ ዞሮ በመሳቅ እያየ/ የእግዚአብሔር ፍርዱን ማን ይመረምረዋል! አሁን ይህን እምነት በላ፣ ውርስ በላ፣ ወገን በላ ማን እንዲህ ይሆናል ብሎ አስቦ ነበር፡፡

**ለገሰ፡-** ቀጥል አሁንም ሌላ ካለህ!

**ዕዝራ፡-** ሞት በሥጋ ውዳቂ ነው! አንፈራም በላት ለሴት አለቃህ! /ፊቱን ወደ አስቴር አዙሮ/ ብቸኝነት ፈጀኝ፣ ለበለበኝና ልሞት መጣሁ፡፡ አይዞሽ አስቴር በርቺ፡፡ እነቤቴልን፣ እነአባባን እናገኛቸዋለን፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ክርስቶስንና እመቤታችንን እርገኛቸዋለን ፡፡ /ፊቱን ወደ ህዝቡ መልሶ/ ያልረባ ዘመን አመጣሽ እምነት ይጠፋል፤ እውነተኛና ቀጥተኛ የሆነች ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ግን በሰማዕታት ደም ትፈካለች፡፡ ወገኖች መጠራታችሁን ተመልከቱ፡፡ እንደሰው ጥበብ ጥበበኞች የሆኑ ብዙዎች፣ ኃያላን የሆኑ ብዙዎች፣ ባላባት የሆነ ብዙዎች አልተጠሩም፡፡ ሥጋን የለበሱ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ፡፡

**ለገሰ** ፡- በቃህ ዝጋ! /ሰይፍን ይዘረጋበታል/

**ዕዝራ፡-** ሰይፋን የሚያነሱ በሰይፍ ይወድቃሉ፤ ሰይፍህን እንደ ጓደኛህ ወደ አፎቱ ብትመልስ ይሻልሃል፡፡

**ለገሰ፡-** ማነህ ---- ደምስ ና ወዲያ ውሰድልኝ ---- እንዲያውም ቆይቆይ ተወው እኔው እራሴ እቶን ውስጥ እማግደዋለሁ፡፡ አንተ እነርሱን ወሰደህ አንገታቸውን በሰይፍ ቅላቸው፡፡

**ካሌብ፡-** ወንድሞቼና እህቴ ይቅር በሉኝ በሰማይና በምድር በፊታችሁ በደልኩ የሥጋ ፍላጐቴ ይመቻችልኝ መስሎኝ ለሃብት ስል ሸጥኳችሁ፡፡ እንደዴማስ ጠፍቼ፣ እንደይሁዳ ሞቼ፣ እንዳልቀር እባካችሁ ስለመድኃኔዓለም፣ ስለ እመቤታችን ፣ ስለቅዱሳን መላእክት ስለ ጻድቃን ሰማዕታት ብላችሁ ይቅር በሉኝ፡፡

**ሶምሶን፡-** አይዞህ ካሌብ ፀፀት ንስሐ ነው፡፡ እንኳንም መበደልህ ተሰማህ እንጂ ይቅር ብለንሃል፡፡

**አስቴር፡-** ተነሰ ወንድሜ የኛ ኃዘናችን የነበረው እኛን መበደልህ ሳይሆን ጠፍተህ መቅረትህ ነው፡፡ አሁን ግን እንደ ፊያታዊ ዘየማን በዝች ባለቀች ሰዓት ወደ ሞት ስንነዳ መመለስህ በጣም አስደስቶናልና ይቅር ብለንሃል፡፡

**አብነት፡-** ወደ ሰማይ እየተመለከተ እማማ አበባ በሰይፍ ያለቃችሁ ወገኖች ደማችሁ ጉልቶ ታየኝ፣ ድምፃችሁ አካል ነስቶ ተሰማኝ፣ ብክደው ሊከደኝ ፣ ብይዘው ሊያፅናናኝ የሰጣችሁኝን ውርስ ለማን ላስረክበው? /ወደ ሕዝቡ ዞሮ/ ንገሩኝ እስኪ አባቴ እውን ሞተ? እማማ እውን ተለየችኝ? አጐቴስ ቆዳው ተገፈፈ? እስኪ ንገሩኝ? እዝራ ብናኝ ሆነ? እነ አስቴር ፣ እነ ቤቴል የትገቡ? ንገሩኝ እንጂ? በሉ ንገሩኝ?

**ተመልካቹ፡-** ሁሉም ሞተዋል!

**አብነት፡-** አልሞቱም በፍጹም አልሞቱም! በርግጥ በሥጋ ሞተዋል፡፡ እኔ ግን አገኘሁአቸው፡፡ /ወደ ውርሱ እየተመለከተ/ አዎ አገኘሁአቸው፡፡ የመሞታቸው ምሥጢር በደማቸው ከትበው ለእኛ ያስተላለፉትን ይህ ንዋየ ቤተክርስትያን ንዋየ ኢትዮጵያ ነው፡፡ /ወደ ህዝቡ ዞሮ/ አንተ የአባቴ ቡቃያ እዳ አለብህ፣ የእነ አበባ የሞት እዳ የነ አበባ የውርስ እዳ፣ ማነው የአባባን የውርስ እዳ የሚጠብቅ? አንተ በቃያ ሰይጣን መጥፎ ዘርን ሊዘራብህ ክህደት ሊጠናወትህ ተነስቷልና ላትክድ ቃል ግባ፡፡........ /ዳዊቱን አንስቶ/ አንተ ዳዊት እስ ተናገር በክበሮ በጸናጽል በመሰንቆ በበገና ማለትህን እውነቱ ጠፍቶበት፣ በጊታር ፣በኦርጋን፣ በጃዝ ፣በሳክስፎን ለሚመለው ለዚህ ትውልድ እስኪ አስረዳው፡፡ /መቋሞያውን አንስቶ/ አባቴ ቅዱስ ያሬድ አቋቋምህ ፣ ዝማሬህን ፣ ዝማሜውን፣ መርግዱን እውነት ጠፍቶበት በዳንስ ለለወጠው ለዚህ እኩይ ትውልድ እስ አሳይ .... አንተ ትውልድ /ወደ ውርሱ እያመለከተ/ ይህንን ብትይዘው ያበራልሃል፤ ብትለቀው ግን ሕይወትህ በሙሉ ይጨልምብሃል .... ለዘለዓለማዊ ቤትህ ስንቅ ቋጥር፡፡ /ውርሱን እያሳየ/ አገልግሉም ያው፣ ምግቡም ያው፤ አበላሉን ግን እውቅበት ... አደረ አለባችሁ ተረካቢዎች እናንተ ናችሁ፤ ብክደው ይካደኝ ብተወው ይተወኝ! የያሬድ አምላክ ...በማለት ለራሳችሁ ቃል ገብታችሁ ውርሱን ተረከቡኝ በሉ ተረከቡኝ! ............

**ተፈጸመ**